# ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መጽሄት

# Debre Markos University News letter

በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
በየሦስት ወር የሚታተም

Quarterly Newsletter
Published by the Corporate
Communications Directorate

ቅጽ-2 ቁጥር-16 ከሐምሌ 2005 - መስከረም 2006 ዓ.ም Volume-2Number- 16 Julay- September 2013


## ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለመምህራንና ሰራተኞች የማበረታቻ ሽልማት ሰጠ

ደማዩ፡- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2005 ዓ.ም. በጀት አመት የላቀ አፈፃፀም ውጤት ላስመዘገቡ አመራሮች፣ መምህራንና ሠራተኞች የማበረታቻ ሽልማት ሠጠ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተቋማዊ ለውጥ ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ ታፈረ መላኩ እንደገለፁት የማበረታቻ ፕሮግራሙ ዓላማ የላቀ አፈፃፀም ላሣዩ አመራሮች፣ መምህራንና ሰራተኞች ተገቢውን እውቅና ለመስጠትና በማህበረሰቡ ዘንድ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲውን የ2006 ዓ.ም. እቅድም በላቀ መልኩ ለመፈፀም ፋይዳው የጐላ ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የተሸለሙት ለበለጠ ውጤት የሚጥሩበት ሽልማቱን ያላገኙት ደግሞ ተፎካካሪ ሆነው ስራቸውን የበለጠ አድምተው በመስራት በተነሳሽነት ለተሸላሚነት የሚበቁበትን መድረክ የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡ በመሆኑም የማበረታቻ ሽልማቱን እንደ ስርዓት ለመትከል መመሪያ 4 ወጥቶ በሴኔት መጽደቁንና አጠቃላይ ሂደቱ በመመሪያው መሠረት መፈፀሙን አያይዘው ገልፀዋል፡፡ የተሻላ味ች ምልመላ ሁሉን ያሳተፈ በመሆኑ የማበረታቻ ሂደቱ በሁሉም ዘንድ ይሁንታ አስገኝቷል ብለዋል፡፡



ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ ሽልማት ሲሰጡ

ሽልማት ያገኙት የዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣ መምህራንና ሠራተኞች የተመረጡት በቅድሚያ ከዩኒቨርሲቲው ዕቅድ ካስኬድ እየተደረገ በያዙት የግለሠብ ዕቅድ የላቀ አፈፃፀም ያላቸውና በሴኔቱ በፀደቀው ተጨማሪ መስፈርት የላቀ ውጤት ያስመዘገቡት መሆናቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዚህም 56 መምህራን፣ 21 የአስተዳደር ሠራተኞችና 7 አመራሮች በድምሩ 84 ግለሰቦች በ2005 ዓ.ም. የላቀ የአፈፃፀም ውጤት በማስመዝገብ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የፋይናንስ ኦፊሰር ወ/ሮ እናቴነሽ አስረስ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከአስተዳደር ሰራተኞች 1ኛ በመውጣት የብር መዳሊያ ተሸላሚዋ እንደገለፁት በ2005 ዓ.ም. የስራ አፈፃፀም የላቀ ውጤት አስመዝግበው ተሸላሚ መሆናቸው በጣም ደስታን የፈጠረላቸው ከመሆኑ ባሻገር ለወደፊቱ የበለጠ ለመስራት ያነሳሳቸው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ሽልማቱም በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ዘንድ የውድድር መንፈስ በመፍጠር ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለተሻለ ስራ እንዲተጋ ያደርጋል ብለዋል፡፡ አያይዘውም ተሸላሚዎቹ የተመረጡበት አግባብ ከየክፍሉ ባሉ ሠራተኞችና የበላይ ሃላፊ በመሆኑ መረጣው ስራን ያማከለና ፍትሃዊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉደይ ም/ፕሬዚዳንት የሆኑት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ እንደገለፁት የዛሬው ሽልማት በ2005 ዓ.ም. የላቀ አፈፃፀም ውጤት ያስመዘገቡትን ሠራተኞች እውቅና የምንሰጥበት ለበለጠ ውጤት ለመስራት የምንነሳበት ነው፡፡ በመሆኑም በሚቀጥለው ዓመት ሌሎች ተሸላሚዎችን የምናይበት በቁጥርም የተሻለ የሚሆንበት ዓመት እንደሚሆን ጠቁመዋል፡፡ ለዚህም ሁላችንም ለተሻለ ውጤት ጠንክረን እንስራ የሚል መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

## በውስጥ ገፆቻችን


- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለመምህራንና ሰራተኞች ማበረታቻ ሰጠ ……………………………………1
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች አስመረቀ…………………2
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የትብብር ስምምነት ተፈራረመ……………………………………………2
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የጋራ መግባቢያ ተፈራረመ……………………………………………3
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለክረምት ተማሪዎች ኦረንቴሽን ሠጠ ………………………………………4
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የእግር ኳስ ቡድን ብሄራዊ ሊጉን ተቀላቀለ……………………………………5
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የጋራ መግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ……………………………………………6
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለ2ኛ ደረጃና መሰናዶ ተማሪዎች ስልጠና ሰጠ ………………………………7
- የ2005 ዓ.ም. የአፈፃፀም ግምገና የ2006 ዓ.ም. እቅድ ትውውቅ ተካሄደ…………………………………8
- 6ኛው ብሄራዊ የሰንደቅ አላማ ቀን በዓል ተከበረ… 8
- የህይወት ክህሎት የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጠ……. 9
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቡሬ ካምፓስ አዲስ ተማሪዎችን ተቀበለ……………………………………10
- ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና ሰራተኞች ስልጠና ተሰጠ …………………………………… 11
- አዲስ ለተቀጠሩ እና ትምህርት አጠናቀው ለተመለሱ መምህራን ስልጠና ተዘጋጀ……………………………11
- ለዩኒቨርሲቲ ፓሊሶች የአቅም ማጐልበቻ ስልጠና ተሰጠ……………………………………………12
- በብዝሃነትና አክራሪነት ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ ……………………………………………………13



0913-94-87-23 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: ermy202699@yahoo.com Website: www.dmu.edu.e

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች አስመረቀ

**ደ/ማ/ዩ፡-**ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በስድስት ኮሌጆች በአንድ ትምህርት ቤት በተለያዩ የትምህርት መስኮች ያሰለጠናቸውን ከ1,700 በላይ ተማሪዎችን ሰኔ 29 ቀን 2005 ዓ.ም. ለ5ኛ ጊዜ በደማቅ ሁኔታ አስመረቀ፡፡



አቶ ይልቃል ከፋለ የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት አቶ ይልቃል ከፋለ እንደገለፁት፣ የ2005 ዓ.ም. የምረቃ ስነ-ስርዓት ለመጀመያ ጊዜ 147 በምህንድስና የትምህርት ዘርፍ በመጀመያ ዲግሪ እና 11 የሁለተኛ ዲግሪ ተመራቂ ተማሪዎችን ማካተቱ ከዚህ በፊት ከነበሩት የምረቃ ስነ-ስርዓቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡ እንደ ፕሬዝዳንቱ ገለጻ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተቀበላቸውን ተማሪዎች በስርዓተ ትምህርቱ የተቀረፀውን ዓላማና ይዘት በሚገባ በመተግበር ብቁና ተወዳዳሪ ባለሙያ አድርጎ ለማውጣት የሚያስችሉ ስራዎችን ለትምህርት ጥራት ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የአማራ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳደር፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊና እና የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ብናልፍ አንዷለም በበኩላቸው በሐገራችን እየተንሰራፋ ያሉት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዛሬ የሚያደርጉት ማንኛውም የማሠልጠንና የማስተማር ተግባር የነገዋን ሀገር እጣ ፈንታ የሚወስን ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ቀጣዩ የሐገራችን እድገት የሚረጋገጠው ጥራቱና ተገቢነቱ በተረጋገጠ የትምህርት ስርዓት ተቀርጸ በሚወጣ ትውልድ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ሁሉም ሊረባረብ ይገባል በማለት ተናግረዋል፡፡

በመጨረሻም ተመራቂ ተማሪዎች እንደገለፁት ሳይማር ያስተማራቸውን ማህበረሰብና የሀገራቸውን አደራ ለመወጣት ስራ ጠባቂዎች ሳይሆኑ ያካበቱትን ዕውቀትና ክህሎት ተጠቅመው ስራ ፈጣሪዎች በመሆን ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የስራ ዕድል ለመፍጠርና ሀገራቸው የጣለችባቸውን አደራ ለመወጣት ዝግጁ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዩኒቨርሲቲው ከተመረቁት 1700 በላይ ተማሪዎችን ከ400 በላይ ሴቶች ሲሆኑ 147ቱ ከቴክኖሎጂ ኮሌጅ በምህንድስና ትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂዎች መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የትብብር ስምምነት ተፈራረመ

**ደ/ማ/ዩ፡-** ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከስዊዲን መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ከሂውማን ብሪጅ ኢትዮጵያ ጋር ባዮሜዲካል ኮሌጅ በደብረ ማርቆስ ለመክፈት የትብብር ስምምነት ተፈራረመ፡፡



ስምምነቱን ሲፈራረሙ

የትብብር ስምምነቱ ዓላማም በባዮሜዲካል የትምህርት ዘርፍ ብቁ የሆኑ ባለሙያዎችን ለማፍራት የህክምና መሳሪያዎችን አተካከል፣ አጠቃቀም፣ አያያዝና ጥገና ላይ ያለውን የዕውቀት ክፍተት ለመሙላትና የባዮሜዲካል ቁሳቁሶችን ለማሟላት የሚያስችል ነው፡፡ ይህም የህሙማኑን ደህንነት በመጠበቅ የሆስፒታሎችን የህክምና ብቃትና ጥራት በማሻሻል እንዲሁም መንግስት በዘርፉ የሚያወጣውን ከፍተኛ ወጭ በማዳን ማህበረሰቡንና ባለሙያዎችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ተገልጿል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ትብብርና አጋርነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጐጃም አደመ እንደገለፁት ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የትብብርና አጋርነት መስኩን የበለጠ በማጐልበት በናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ የጀመረውን የጋራ መግባባት ውል ስምምነት አጠናክሮ ከሂውማን ብሪጅ ኢትዮጵያ ጋር የትብብር ስምምነት መፈፀሙ ተገቢና ለዩኒቨርሲቲውም ሆነ ለማህበረሰቡ ዕደገት ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ዳይሬክተሩ አያይዘውም ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለሠራተኞች እንዲሁም ለማህበረሠቡ የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎችን እየሰጠ መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

በትብብር ስምምነቱ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶች፣ ዲኖችና ዳይሬክተሮች የተገኙ ሲሆን ከሂውማን ብሪጅ ኢትዮጵያ ደግሞ የሂውማን ብሪጅ ኢስት አፍሪካ ፕሮጀክት አስተባባሪና የኢትዮጵያ ዳይሬክተር የሆኑት አቶ አንለይ አዳሙ፣ የሂውማን ብሪጅ አማካሪ አቶ አላን ካርልሰንና ቦግራንድ ሰን ተገኝተዋል፡፡

በመጨረሻም ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የወሠዳቸውን የጋራ መግባባትና ትብብርነት ውሎች ትኩረት ሰጥቶና አጠናክሮ እንደሚቀጥል የትብብር ስምምነቱም ለስድስት ዓመታት እንደሚቆይና እንደ ሁኔታው ሊታደስ እንደሚችል ለማወቅ ተችሏል፡፡

## ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የጋራ መግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ

**ደ/ማ/ዩ**፡- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ ጋር አብሮ ለመስራት የሚያስችለውን የጋራ መግባቢያ ውል ስምምነት ተፈራረመ፡፡



የውል ስምምነት ሲያካሂዱ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ትብብርና አጋርነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ አቶ ጐጃም አደመ እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲው ከናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ ጋር የጋራ መግባባያ ውል ስምምነት መፈፀሙ ዩኒቨርሲቲያችን የካበተ ልምድ ካለው ከናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ ብዙ ልምዶችን ለመካፈል እንደሚያስችለው ገልፀዋል፡፡

ስምምነቱ ሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ የምርምር ስራዎችን፣ የተማሪዎችና የመምህራን ዝውውር፣ የትምህርት፣ የባህልና የቴክኖሎጂ ልውውጥ ለማድረግ አመች ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የሁለቱ ሀገራት ዩኒቨርሲቲዎች ስምምነት በአንድ አህጉር ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ የባህል ልውውጥ ለማድረግ ከማስቻሉም በላይ ባህላቸውን የበለጠ ለማጐልበትና ተማሪዎችና መምህራንን ተጠቃሚዎች በማድረግ ባህላቸውን ለማጐልበት የሚያስችላቸው መሆኑ ተገልጿል፡፡

በስምምነቱ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶች፣ ዲኖችና ዳይሬክተሮች ሲገኙ ከናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ የሶሻልና ሂውማኒቲስ ሳይንስ ኮሌጅ ፕሪንሲፓል ፕሮፌሰር ንጅሩ ኢኖስ ኤች ኒቲያ እና የአርትስ ፋካልቲ አሶሽየት ዲን ፕርፌሰር ፒተር ዋሳምባ ተገኝተዋል፡፡



ተሳታፊዎች በከፊል

ሁለቱን ሀገራት ወክለው የተሳተፉት አካላትም በጋራ ስምምነቱ ላይ ሰፊ ውይይት ያደረጉ ሲሆን ጥናትና ምርምሮችን በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸው መሆኑ ተገልጿል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተሳታፊዎችም የጋራ ውል ስምምነቱ የሁለቱ ሀገራት ተማሪዎች የባህል ልውውጥ እንዲያደርጉ ከማስቻሉም በተጨማሪ ተማሪዎቹ ሰለባህላቸው ጥናትና ምርምር በማካሄድ ባህላቸውን እንዲያጐለብቱ ለማድረግ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በስርዓተ ትምህርት የልምድ ልውውጥ ለማድረግና በተማሪዎች መካከል የውድድር መንፈስ ለመፍጠር ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ገልፀዋል፡፡

## ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለክረምት ተማሪዎች ኦረንቴሽን ሠጠ

**ደ/ማ/ዩ**፡- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለ2005 ዓ.ም. የመጀመሪያ ዓመት የክረምት ተማሪዎች የግቢና የአሠራር ስርዓት ትውውቅ አደረገ፡፡



ለክረምት ተማሪዎች ትውውቅ ሲካሄድ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተከታታይ ትምህርት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ይኸይስ አረጉ እንደገለፁት የኦረንቴሽኑ ዓላማ ተማሪዎች ለግቢው እንግዳ በመሆናቸው በተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች የሚሠጧቸውን አገልግሎቶች፤ በቆይታቸው ሊያከብሯቸው የሚገቡ ስነ ስርዓቶችንና ህጐችን በተመለከተ ዕውቅና ለመፍጠር ነው፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ አስቻለው ታደገ እንደተናገሩት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ቆይታቸው አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን እንደሚያገኙ ገልፀዋል፡፡

በአስተዳደራዊ አገልግሎቱም ዩኒቨርሲቲው ከፕሬዚዳንት እስከ ዲፓርትመንት ድረስ የራሡ አደረጃጀት ያለው መሆኑን ገልፀው የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬትም በአስተዳደራዊና ተማሪዎች ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ስር ያለ መሆኑን ጠቅሠው 25 ያህል አገልግሎቶችን እንደሚሠጡ ገልፀዋል፡፡

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ ዲን አቶ ፈቃዴ መንግስቴ በበኩላቸው ተማሪዎቹ አሁን እንደ መምህር ሳይሆን የሚስተናገዱት እንደ ተማሪ በመሆኑ የተማሪ ስነ ስርዓትን በመላበስ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የተሻለ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን በሚገባ በመከታተል በየትምህርት ዘርፋቸው ለተሻለ ውጤት መስራት እንዳለባቸውና የዩኒቨርሲቲውን ሀብትና ንብረት በመንከባከብ በኩል የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ ቀርቧል፡፡

## የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የእግር ኳስ ቡድን ብሄራዊ ሊጉን ተቀላቀለ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የእግር ኳስ ክለብ በድሬዳዋ ከተማ በ27 ክለቦች መካከል ሲካሄድ በነበረው ውድድር ወደ ብሔራዊ ሊግ ከገቡ 7 ክለቦች ውስጥ የአማራ ክልልን በመወከል ብሔራዊ ሊጉን ተቀላቀለ፡፡



አቶ ይልቃል ከፋለ ንግግር ሲያደርጉ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት አቶ ይልቃል ከፋለ ክለቡ ምቹ ሁኔታ ሳይፈጠርለት የቡድኑ መሪዎች፣ አሠልጣኞችና ተጫዋቾች በራሳቸው ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ስፖርቱን በመውደድ ባደረጉት ጥረትና የመናበብ ስራ ያመጡት ውጤት በመሆኑ የዩኒቨርሲቲያችንንና የከተማችንን ማህበረሰብ በከፍተኛ ሁኔታ ያኮራና ያስደሠተ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

እንደ ፕሬዝዳንቱ ገለጻ፣ ስፖርት በአሁኑ ወቅት ጤና፣ ብቃትና ገንዘብ ስለሆነ ይህንን ውድ የሆነ ሃብት በመንከባከብ ማሳደግና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ የዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣ የከተማችን ማህበረሠብ ኃላፊነት ነው፡፡ በመሆኑም ክለቡን በማደራጀት፣ በማስተባበር ስፖርት በአካባቢው ነፍስ እንዲዘራበት፣ የተለያዩ ክለቦች መጥተው እንዲጫወቱ፣ ወጣቶች የሚዝናኑበት መድረክ እንዲኖር እናደርጋለን ብለዋል፡፡

በብሄራዊ ሊግ ክለብ ውስጥ ግንባር ቀደም ተጫዎቾች የሚፈልቁበትና በዓለማችን የሚታዩ ተጫዋቾች የሚወጡበት ክለብ እንደሚሆን እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡



አቶ ምንውየለት አሠፋና ታዳሚዎች

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የእግር ኳስ ቡድን መሪ አቶ ምንውየለት አሠፋ ክለቡ ለብሄራዊ ሊግ ሊያልፍ የቻለው ብዙ ትግሎችን አድርጐ በመሆኑ ጥረቱን አጠናክሮ በሚቀጥለው ዓመት ወደ ፕሪሚየር ሊግ እንደሚገባ እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ ቡድን መሪው እንደገለፁት ክለቡ በምስራቅ ጐጃም ዞን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ወደ ብሔራዊ ሊግ የገባው በዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣ ማህበረሠብና ተጫዋቾች ባደረጉት ከፍተኛ ጥረት ነው፡፡

የምስራቅ ጐጃም ዞን ስፖርት ኮሚሽን ኃላፊ የሆኑት አቶ ውብሸት ልንገር በበኩላቸው የእግር ኳስ ክለቡ በ2004 ተቋቁሞ በ2 ዓመት ውስጥ ለከፍተኛ ውጤት የበቃው በዩኒቨርሲቲው ማህበረሠብ፣ በክለቡ መሪዎች፣ በአሠልጣኞችና በተለይም በስፖርተኞች ጥረት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሚሠራቸው ስራዎች በርካታ ቢሆኑም ክለቡን ከ14 የፕሪሚየር ሊግ ክለቦች እንዲቀላቀል በማድረግ ዩኒቨርሲቲዉንና ወጣቶችን በስፖርቱ

ከፍተኛ ተጠቃሚ በማድረግ የአካባቢያችንን ገጽታ ማስተዋወቅ እንዲችል የምስራቅ ጐጃም ዞን ስፖርት ኮሚሽን የበኩልን አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡



የአቀባበሉ ክፊል ገጽታ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አባላትና የደብረ ማርቆስ ከተማ ማህበረሰብ ለእግር ኳስ ቡድኑ ደማቅ አቀባበል አድርገውለታል፡፡

## ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የጋራ መግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በማስተማር፣ ምርምር እና በማህበረሠብ አገልግሎት በጋራ ለመስራት የሚያስችለውን ስምምነት ነሀሴ 16/2005 ዓ.ም. ተፈራረመ፡፡




የመግባቢያ ሰነዱን ሲፈራረሙ

አቶ ይልቃል ከፋለ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዩኒቨርሲቲያችን አዲስ በመሆኑ ትልቅ አቅምና ልምድ ካለው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጮቄ ተራራ ጥናትና ምርምር ለማድረግ ስምምነት ማድረጉ ትልቅ አቅም ለመፍጠር ያስችለናል ብለዋል፡፡

የጮቄ ተራራ ምርምር ለአካባቢያዊ ልማት ብቻ ሳይሆን ክልላዊና ሀገራዊ ፋይዳው የጐላ ነው፡፡ ምርምሩ በምስራቅ አፍሪካና በሰሜን አፍሪካ ትልቅ አቅም የሚፈጥር በመሆኑ የተናጠል ጉዞ ጥቅም ስለሌለው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር ለማካሄድ የጀመሩትን ትብብር አጠናክረው ለመሄድ የመምህራኑም ሆነ የአመራሩ ቁርጠኝነት መኖሩን ጠቁመዋል፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር መርሻ ፊጠነ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ስምምነቶችን ከብዙ የውጭ ሀገራት ጋር ሲያካሂድ የቆየ ቢሆንም ከአገር ውስጥ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የሚታሰበውን ያህል እንዳልነበረ አስታውሰው ከሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በምርምር ስራዎች ቢሳተፍ ለሀገሪቱ ዕድገት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው በመግለጽ ለመጀመሪያ ጊዜ የትብብር ስምምነቱ ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጋር መፈረሙን ተናግረዋል፡፡

ፕሮፌሰሩ አያይዘውም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጮቄ ተራራ ላይ ከ2 እና ከ3 ዓመታት በፊት በግሉ ምርምር ሲያካሂድ መቆየቱን አስታውሰው በአሁኑ ሰዓት ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በባለቤትነት በመያዝ በምርምሩ ላይ ሊሠራ የሚገባው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ስምምነቱም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን በሀገሪቱ ዋና የዕድገት ጉዳይ ላይ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚያስችለው የወደፊት የምርምርና የስምምነት ማዕቀፍ በመሆኑ ትልቅ ቦታ እንሠጠዋለን ብለዋል፡፡

የጮቄ ተራራ ፕሮጀክት አስተባባሪ የሆኑት ዶ/ር በላይ ስማኔ በበኩላቸው ባለፉት ዓመታት በግል ብዙ ሲሠራ ቢቆይም የጮቄ ተራራ የክልሉን የአየር ሁኔታ የሚቆጣጠር በመሆኑ በጋራ የሚሠራ ምርምር የሀገሪቱን የልማት ጉዞ ዕውን ለማድረግ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ገልጸዋል፡፡ የጮቄ ተራራ ምርምር በግብርና ብቻ ሳይሆን ሁሉን አቀፍ ለማድረግ የታሠበ ነው፡፡ በመሆኑም በምርምሩ ሁሉም ተመራማሪዎች ለሀገሪቱ የዕድገት ጥሪ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡



ተሳታፊዎች በከፊል

በመጨረሻም ስምምነቱ ለአራት ዓመታት የሚቆይና እንደሁኔታው የሚታደስ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለ2ኛ ደረጃና መሰናዶ ተማሪዎች ስልጠና ሰጠ

**ደ/ማ/ዩ፡-** ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ተሰጥኦ ላላቸውና በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ የ2ኛ ደረጃና መሠናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት አይነቶች ስልጠና ሠጠ፡፡



ተማሪዎች በክፍል ውስጥ

የስልጠናው ዓላማ በሳይንስና ቴክኖሎጅ ከፍተኛ ችሎታ ላላቸው የመጀመሪያ፣ የ2ኛ ደረጃና የመሠናዶ ተማሪዎች በክረምት ወቅት በተግባር የተደገፈ ትምህርት ለመስጠት፤ በ2ኛ ደረጃና መሠናዶ ትምህርት ቤቶች የሚሠጡ ትምህርቶችን ጥራት ለመሻሻል፣ ከተለያየ ቦታና ባህል የሚመለመሉ ተማሪዎች እርስ በእርስ የመተዋወቅ፣ የመማርና የመቻቻል ባህል እንዲያዳብሩ ለማገዝና የተማሪዎችን እርስ በርስ የመማማር ዘዴ ደጋፊዎችንና ፈፃሚዎችን ለማፍራትና አቅም ለመጨመር መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ስልጠናውን ያዘጋጀው የመንግስትን አቅጣጫ በመከተል በሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት አይነቶች ልዩ ተሠጥኦ ላላቸው የሁለተኛ ደረጃና የመሠናዶ ተማሪዎች ሲሆን ፕሮግራሙም በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት በማህበረሠብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት አስተባባሪነት የሚተገበር STEM Center (ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጅነሪንግ እና ሒሣብ) በሚል ስያሜ በማቋቋም የክረምት ማበልፀጊያ ፕሮግራም መሆኑን በማህበረሠብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የስልጠናና ማማከር ኦፊሰር የሆኑት አቶ ሙሉጌታ ተስፋ ጠቁመዋል፡፡

ሰልጣኞች ስልጠናውን የተከታተሉት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሙሉ አገልግሎት ተሟልቶላቸው ሲሆን ከመደበኛ ስልጠናቸው በተጨማሪ የህይወት ክህሎት፣ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ መከላከል እና የመልካም ስነ ምግባር ስልጠና እንዲሁም የምክር አልግሎት መውሰዳቸው ተገልጿል፡፡

ሰልጣኝ ተማሪዎች የተመለመሉት ከደብረ ማርቆስ ከተማ ወረዳ እና ከጐዛምን ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች ሥር ከሚገኙ የሁለተኛና የመሠናዶ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡

በስልጠናው 128 ወንድ እና 27 ሴት በድምሩ 155 ተማሪዎች በተግባር የተደገፈ የአይ.ሲ.ቲ፣ የፊዚክስና የሂሣብ ትምህርት የአንድ ወር ስልጠና ወስደዋል፡፡

## የ2005 ዓ.ም. የሥራ አፈፃፀም ግምገማና የ2006 ዓ.ም. እቅድ ትውውቅ ተካሄደ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መምህራን እና ሰራተኞች የ2005 ዓ.ም. እቅድ አፈፃፀም ግምገማና የ2006 ዓ.ም. እቅድ ትውውቅ ተካሄደ፡፡



የውይይቱ ሂደት ከፊል ገጽታ

እንደ ዩኒቨርሲቲው የእቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ አብዩ ተጐዳ ገለፃ የ2005 ዓ.ም. እቅድ አፈፃፀም በአጭርና በረጅም ጊዜ የሚፈቱ ችግሮችን በመለየትና በመፍታት አገልግሎት አሰጣጡ ደንበኞችን እንዲያረካ ተደርጓል፡፡ የምርምር ስራዎችም ሀገራዊና ተቋማዊ የትኩረት አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ ተሰርተዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲው የትምህርት ልማት ሰራዊት ለመገንባት የአንድ ለአምስት አደረጃጀት በየትምህርት ክፍሉ በማቋቋም የተማሪዎች የርስ በርስ መተጋገዝና ውጤታማነት እንዲጐለብት፣ የዩኒቨርሲቲውን ገቢና ወጭ ለመቆጣጠር የአይቤክስ ምዝገባ፣ ገቢ እየተሰበሰበባቸው ያሉ ተግባራትን አጠናክሮ የማስቀጠል ስራ እንዲሁም የትምህርት ጥራትና አግባብነት ፓሊሲን በአግባቡ በመተግበር የሚሰጠው ትምህርት ጥራቱንና አግባብነቱ የተሻለ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

እንደ ዳይሬክቶሬቱ ገለጻ የመማር ማስተማር ስርዓቱ አሳታፊ ለማድረግም ተማሪ ተኮር የሆነ ስልጠና በመተግበር ተማሪዎችን የመደገፍና የማብቃት ስራ ተሰርቷል፡፡ የመምህራንና ሰራተኞችን አቅም ለማሳደግ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ የተሠራ ሲሆን የግንኙነት ስራዎችም በህትመቶች፣ በዌብሳይት እና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በመሳሰሉት ተሰርተዋል፡፡ በአጠቃላይም በውይይቱ በእቅድ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች፣ የነበሩ ድክመቶችና የተሰጡ መፍትሄዎች ተገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም የ2006 ዓ.ም. እቅድ ሲዘጋጅ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን፣ የዩኒቨርሲቲው የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ እቅድና በ2005 በጀት አመት እቅድ አፈፃፀም የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ መሆኑን የገለፁት ዳይሬክተሩ የለውጥ ፕሮግራሞችን ማስቀጠል የበጀት ዓመቱ ቁልፍ ተግባር መሆኑን ገልፀው አስራ ሦስት ግቦችን የያዘ ዝርዝር እቅድም ቀርቦ ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡ ተሳታፊዎችም በቀረበው እቅድ ላይ ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን ያቀረቡ ሲሆን ከመድረክ ማብራሪያና ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 6ኛው ብሄራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን በዓል ተከበረ

**ደማዩ፡-** ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 6ኛውን ብሔራዊ የሠንደቅ ዓላማ ቀን በዓል በፓናል ውይይት አከበረ፡፡

የፓናል ውይይቱ ጽሁፍ አቅራቢዎች መምህር አየነው ማሞ፣ መምህር ምስጋናው ጋሻውና መምህርት ቤተልሔም ባይተሳው የሰንደቅ ዓላማ ምንነትና በትምህርት ተቋማት የሰንደቅ ዓላማ

ቀን ማክበር አስፈላጊነት፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሰንደቅ ዓላማ አዋጅና የሠንደቅ ዓላማ እሴቶች በኢትዮጵያ በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች የመነሻ ጽሁፍ አቅርበዋል፡፡



አወያዮች ጽሁፋቸውን ሲያቀርቡ

መምህር አየነው ማሞ የሰንደቅ ዓላማ ምንነትና በትምህርት ተቋማት የሰንደቅ ዓላማ ቀን ማክበር አስፈላጊነትና ዓላማ ላይ ጽሁፍ ያቀረቡ ሲሆን በሰንደቅ ዓላማ እሴቶች፣ መገለጫዎች፣ ታሪካዊ ዳራና አለማቀፋዊ ልምድ እንዲሁም የበዓሉን ፋይዳ በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

መምህር ምስጋናው ጋሻው በበኩላቸው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ የሠንደቅ ዓላማ አዋጅ 654/2001 ላይ የመወያያ ጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ በዚህም የሠንደቅ ዓላማ ምንነት፣ ቀለማትና ቅርጽ፣ መጠንና አጠቃቀም፣ ሥነ-ስርዓት፣ በሠንደቅ ዓላማ ሥነ-ስርዓት የተከለከሉና ቅጣት የሚያስከትሉ ተግባራት እንዲሁም ስለብሔራዊ መዝሙር ምንነት፣ አጠቃቀምና የስነ ስርዓት ደንቦች ክልከላዎች ላይ ሠፊ ገለፃ አቅርበዋል፡፡

መምህርት ቤተልሔም ባይተሳው በበኩላቸው የአዲሲቷን ኢትዮጵያ የሠንደቅ ዓላማ እሴቶች፣ የእምነትና የሀይማኖት ነፃነትና እኩልነት በአዲሲቷ ኢትዮጵያ፣ የሠንደቅ ዓላማ እሴቶችን በመጠበቅ የወጣቶችና የሴቶች ሚና በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች የውይይት ጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

በቀረቡት የመወያያ ጽሁፎች ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን ከተሳታፊዎችም ጥያቄዎች ቀርበው በተሳታፊዎችና በአቅራቢዎች ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡



ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ ንግግር ሲያደርጉ

በመጨረሻም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት የሆኑት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ በሠንደቅ ዓላማ ጉዳይ ማንኛውም ዜጋ እንደማይለያይና ሁላችንም ሊያግባቡን በሚችሉ ብሔራዊ ጉዳዮች በጋራ ጠንክረን መስራት ያለብን መሆኑን በመግለጽ የፓናል ውይይቱ ስለ ሠንደቅ ዓላማ የነበረንን ግንዛቤ ያዳበረልን መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

## የህይወት ክህሎት የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጠ

**ደ/ማ/ዩ፡-** ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሁሉም ኮሌጆች ተመርጠው ለመጡ መምህራን የህይወት ክህሎት የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጠ፡፡

የስልጠናው አላማ ዩኒቨርሲቲው በዘንድሮው ዓመት የተቀበላቸውን አዲስ ተማሪዎች ለማሰልጠንና እንዴት ህይወታቸውን መምራት እንዳለባቸው ለማስገንዘብ እንደሆነ ታውቋል፡፡



የስልጠናው ሂደት ከፊል ገጽታ

በስልጠናው ተማሪዎች ራሳቸውን አውቀው ሌሎችንም በማወቅ አብሮ በመኖር ብልሀት፣ ራስን በመገንዘብ፣ በራስ በመተማመን፣ የተግባቦት ክህሎት በማዳበር፣ የአቻ ግፊት በመቋቋም፣ በጊዜ አጠቃቀም፣ እቅድ ማውጣት እና በዕቅድ መመራት በሚሉ ሃሳቦች ዙሪ ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡

ለአምስት ቀናት በቆየው ስልጠና 18 /አስራ ስምንት/ ተሳታፊዎች የተካፈሉ ሲሆን የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሥርዓተ ጾታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስና አካል ጉዳተኞች ዳይሬክቶሬት ስልጠናውን አዘጋጅቶታል፡፡

## የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቡሬ ካምፖስ አዲስ ተማሪዎችን ተቀበለ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በቡሬ ካምፓስ የምደባ ዕጣ የደረሳቸውን 181 ተማሪዎች በማኔጅመንት፣ አካውንቲንክ፣ አግሪ ቢዝነስና ሆርቲ ካልቸር የትምህርት ዘርፎች ለማሰልጠን ለመጀመሪያ ጊዜ መቀበሉ ተገለፀ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቡሬ ካምፓስ ዲን የሆኑት አቶ ጠግቤው ዋለ ተማሪዎቹን እንኳን ወደ ቡሬ ካምፓስ በደህና መጣችሁ በማለት ካምፓሱ ለተማሪዎቹ ምቹ እንደሆነና ሁሉንም አገልግሎቶች ከመጡበት ዕለት ጀምሮ ማግኘት እንደሚችሉና የምግብ ካርድ እንደተዘጋጀላቸው ገልፀዋል፡፡ በዚህም ተማሪዎች እንደገቡ በግቢው የምሳ ግብዣና የመኝታ ክፍሎች ምደባ ተደርጐላቸዋል፡፡



አቶ ጠግቤው ዋለ ተማሪዎችን ሲቀበሉ

አቶ ጠግቤው ዋለ ተቋሙ ተማሪዎችን ለመቀበል ዝግጅት የጀመረው ከ2005 የትምህርት ዓመት ጀምሮ እንደሆነና ዝግጅቱን በክረምት ወቅት እንደጨረሠ ገልፀው ሁሉም ነገር እየተሟላ በመሆኑ ተማሪዎች የሚቸገሩበት ጉዳይ እንደማይኖር ጠቁመዋል፡፡



አቶ ብርሃኑ ታደሰ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ሲያደርጉ

የቡሬ ከተማ ወረዳ አስተዳደር ከንቲባ የሆኑት አቶ ብርሃኑ ታደሰ በበኩላቸው የቡሬ ከተማ ተስማሚ የአየር ንብረት ያላት መሆኑን በመግለጽ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር አድርገዋል፡፡ አያይዘውም ተማሪዎቹ በተቋሙ ቆይታቸው የሚያጋጥሟቸውን ማንኛውንም ችግሮች ለመፍታትና ድጋፍ ለማድረግ ከተማ አስተዳደሩ በቀጣይ ከተማሪዎች ጋር በቅርበት በሚያካሂዳቸው የውይይት ፕሮግራሞች እንደሚገናኙ ገልፀዋል፡፡ ዋናው የአቀባበል ፕሮግራምም በከተማዋ ነዋሪዎች ወደፊት በደማቅ ሁኔታ እንደሚካሄድ ጠቁመዋል፡፡

የቡሬ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ ተሻለ ጥበቡ በበኩላቸው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቡሬ ካምፓስ መከፈት ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢ የሚመጡ ተማሪዎችን የባህልና የታሪክ ትስስር የበለጠ ከማጠናከሩም በላይ ሀገራችን የጀመረችውን የዕድገት ጉዞ በጋራ አጠናክሮ ለመጓዝ ያስችላል ብለዋል፡፡ ይህንንም የፈቀደላቸውን የፌደራሉንና የክልሉን መንግስት ብሎም የዩኒቨርሲቲውን በሳል አመራር እንደሚያደንቁ ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ምንውየለት አሰፋ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በቡሬ ካምፓስ የተቀበላቸውን ተማሪዎች በዕውቀት፣ በአመለካከትና በክህሎት ብቁና ተወዳዳሪ ለማድረግ የመምህራንና ሰራተኛው ሃይል እየተሟላና እየተደራጀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከቡሬ ማህበረሠብ ጋር ለወደፊት የበለጠ ተቀራርበው እንደሚሠሩ ገልጸው የቡሬ ከተማ ማህበረሠብም ላደረገው አቀባበልና የምሳ ግብዣ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

## ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና ሰራተኞች ስልጠና ተሰጠ

**ደ/ማ/ዩ፡-** **ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና ሰራተኞች በብዝሃነት አያያዝ፣ የአክራሪነትና ጽንፈኝነት ዝንባሌዎችና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ፡፡**



የስልጠናው ተሣታፊዎች ከፊል ገጽታ

ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ እንደገለፁት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎቻቸውን ለማሳካት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብም በጉዳዩ መግባባት ላይ መድረስ፣ ሀገራዊ እድገቱን መደገፍ እንዲሁም በአክራሪነትና በጽንፈኝነት ጉዳይ የጋራ አቋም መያዝ አስፈላጊ ነው፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ በአክራሪነትና ጽንፈኝነት ዙሪያ ስልጠናው መሰጠቱ የተለያየ ቋንቋና እምነት ያላቸው ወጣት ተማሪዎች ለአክራሪነት ተጋላጭ እንዳይሆኑና የችግሩን ምንጭ በመረዳት እና ብዛሃነትን በማስተናገድ ችግሩን ለመፍታት ነው ብለዋል፡፡

ስልጠናውን የሰጡት የአማራ ክልል አስተዳደርና ፀጥታ ቢሮ የህዝብ ግንኙት ኃላፊ አቶ አየለ አናውጤ እንደገለፁት የሃይማኖት ብዝሃነት የሀገራችን ተጨባጭ መገለጫ ነው፡፡ እስከ አሁን የነበረን የአይሁድ፣ የክርስትና እና እስልምና ሃይማኖቶች በሀገራችን በሰላም አብሮ የመኖር የቆየ ታሪክም ለአለም ህዝብ የምናበረክተው እሴት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግስትም ባለፉት ስርአቶች የነበረውን የተዛባ ግንኙነት መሰረታዊ በሆነ መልኩ በማስተካከል ለብዝሀነት እውቅና ሰጥቷል፡፡

የዜጎችን የእምነት ነፃነትንና እኩልነትን ለመናድና ሃይማኖታዊ መንግስት ለመመስረት መንቀሳቀስ የአክራሪነት እና ጽንፈኝነት ዝንባሌ ነው ያሉት አቶ አየለ ይህን ችግር ለመፍታት የህገ መንግስት ልዕልናና የሚዛናዊ አስተሳሰብ ትምህርትን ማስፋፋት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ በመጨረሻም ከተሳታፊዎች ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## አዲስ ለተቀጠሩና ትምህርት አጠናቀው ለተመለሱ መምህራን ስልጠና ተዘጋጀ

**ደ/ማ/ዩ፡-** በዝውውር ለመጡ፣ አዲስ ለተቀጠሩና ትምህርታቸውን አጠናቀው ለተመለሱ መምህራን የአራት ቀናት ሥልጠና ተሠጠ፡፡

ሥልጠናውን ያዘጋጀው የዩኒቨርሲቲው ፕሮግራም ቀረፃና ልማት ዳይሬክቶሬት ነው፡፡ እንደ ዩኒቨርሲቲው የስልጠና ኦፊሰር አቶ አፅብሃ ገ/እግዚአብሔር ገለፃ የሥልጠናው ዓላማ መምህራን ስለሞጁላራዜሽን ምንነትና የትምህርት አቀራረብ ግንዛቤ በመፍጠር በአግባቡ እንዲተገብሩ ለማድረግ እንዲሁም የተከታታይ ምዘናን ምንነትና አተገባበር እውቀታቸውን ለማስፋት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንደ እርሳቸው ገለጻ የሥልጠናው መዘጋጀት ስለዩኒቨርሲቲው ህግና አሰራር እውቅና ለመፍጠር፣ የቢ.ኤስ.ሲን ምንነት ለማሳወቅና ስለአሳታፊ መማር ማስተማር ዘዴ ለማስገንዘብ ረድቷል፡፡



የመምህራን ስልጠና ከፊል ገጽታ

እንደ አቶ አፅብሃ ገለጻ ስለሞጁላር ስርአተ ትምህርት አቀራረብና የተከታታይ ምዘና አፈፃፀም እንዲሁም አተገባበር ዙሪያ መምህራን ግንዛቤያቸውን እንዲያጐለብቱ ማድረግ ያስፈለገው በመማር ማስተማሩ ዘርፍ የሚከናወኑ አካዳሚያዊ ሥራዎችን በማከናወን ብቁ ተወዳዳሪና ስራ ፈጣሪ ተማሪዎችን አሰልጥኖ ለማስመረቅ ይረዳ ዘንድ ሳይንሳዊ የትምህርት አቀራረብና የተከታታይ ምዘና ስርዓት ላይ ጥልቅ እውቀት ለማስጨበጥ ነው፡፡

## ለዩኒቨርሲቲ ፓሊሶች የአቅም ማጐልበቻ ስልጠና ተሰጠ

**ደ/ማ/ዩ፡-** ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፓሊሶች የአቅም ማጐልበቻ ስልጠና በደብረ ማርቆስ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ተሰጠ፡፡



የዩኒቨርሲቲው ፖሊሶች በስልጠና ላይ

እንደ ዩኒቨርሲቲው የጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ስማቸው ይግዛው ገለፃ የስልጠናው ዓላማ ዩኒቨርሲቲው ጥበቃ ፖሊስ ክፍል ስብስብ ከፖሊስ፣ ከመከላከያ እና ከሚሊሻ ተቋማት ሲያገለግሉ የነበሩና በተለያዩ ምክንያቶች የለቀቁ እንዲሁም ከሲቪል ማህበረሰቡ ተመልምለው የተቀጠሩ በመሆናቸው በፖሊሳዊ ሙያ የበለጠ ግንዛቤ ያለው የጥበቃ ሰራተኛ መፍጠር ነው፡፡

በስልጠናው የጥበቃ ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ የተቋሙ የጥበቃ ሁኔታ፣ የፍተሻ ምንነት፣ የጥበቃ ፖሊስ ሰራተኞች ስነ ምግባር፣ ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም የግጭት አፈታት ዘዴዎች የሚሉ ሃሳቦች ተዳሰዋል፡፡

በስልጠናው ማጠቃለያ የተገኙት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደርና ተማሪዎች ጉዳይ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ኃይለየሱስ ውዱ ስልጠናው ሰፋ ላለ ሰዓትና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች መሰጠቱ ቀደም ባሉት ጊዜያት ከተሰጡ ሥልጠናዎች እንደሚለይ ገልጸው ተሳታፊዎች ከስልጠናው የተገኙትን ሃሳቦች በማጐልበትና የተሻለ አቅም በመፍጠር የላቀ አፈፃፀም እንዲያስመዘግቡ አሳስበዋል፡፡ በመጨረሻም ስልጠናውን ለሰጡት ኢ/ር ቀለሜ ስርፀ፣ ረዳት ኢ/ር አልማው ወርቅዬ እና ዋና ሳጅን ደርቤ ውድነህ የምስክር ወረቀት አበርክተዋል፡፡ በስልጠናው 86 የዩኒቨርሲቲው ፖሊሶች ለ3 ቀናት መሳተፋቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

# በብዝሃነትና አክራሪነት ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ

**ደ/ማ/ዩ፡-** ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በብዝሃነት አያያዝ፣ አክራሪነትና ጽንፈኝነት ዙሪያ ስልጠና ተሰጠ፡፡

እንደ ዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ ገለፃ ዩኒቨርሲቲዎች የተለያዩ ቋንቋዎች፣ እምነቶችና ማንነቶች ያላቸው በርካታ ወጣት ተማሪዎች መኖሪያ በመሆናቸው፤ የዚህ ስልጠና መሰጠት ተማሪዎች በብዝሀነት ዙሪያ ግንዛቤ ጨብጠው እራሳቸውን ከአክራሪነት እና ከጽንፈኝነት ዝንባሌ በማጽዳት ችግሩን ለመዋጋትና ዓላማቸውን ዳር ለማድረስ ያግዛል ብለዋል፡፡

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ገለጻ ስልጠናው የተማሪዎችን የአክራሪነትና የጽንፈኝነት ግንዛቤ ከማስፋት በተጨማሪ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሁኔታ በመፍጠር የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮዎች ማሳካት ያስችላል፡፡

ስልጠናውን የሰጡት የአማራ ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ቢሮ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ባዝዘው ገላው በበኩላቸው አገራችን የብዙ ብሄሮች፣ ሃይማኖቶች እና ማንነቶች መገኛ መሆኗን ገልፀው ይህ ብዙሀነት ድንቅ እሴታችን መሆኑን እና የኢፌዲሪ ህገ መንግስትም ለብዙሀነት እውቅና መስጠቱን ጠቁመዋል፡፡



ተማሪዎች በስልጠና ላይ

በስልጠናው የአክራሪነትና ጽንፈኝነት ዝንባሌዎችና ስልቶች፣ ሴኩላሪዝምና የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች፣ የአክራሪነትና ጽንፈኝነት አደጋዎች እንዲሁም ችግሩን በአስተማማኝ ደረጃ ለመቅረፍ መስራት ስላለባቸው ስራዎች በስፋት ተዳሷል፡፡

እንደ አቶ ባዝዘው ይህን ድንቅ እሴት ለመናድ፣ የሃይማኖት ነፃነትን ለመጨፍለቅ እንዲሁም መንግስታዊ ሃይማኖት ለመመስረት መንቀሳቀስ የአክራሪነትና ጽንፈኝነት መገለጫ ስለሆነ ልንዋጋው ይግባል ብለዋል፡፡ በመጨረሻም ከተማሪዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተው ምላሽ እና ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡